# ብቀላ

ብቀላ ብጠቁር፤ ብረዝም ባጥርምም
ስደት ቤቴ ሆኖ፤ ደፋ ቀና ብልም
ባህዳን አረቦች፤ ቢሳለቁብኝም
ቡችላው ወያኔም፤ በዘር ቢከፍለኝም
ኢትዮጵያዊነቴን በጭራሽ አልከድም።

ወያኔ ባንዳዎች፤ ቅጥረኞች ተባብረው
አገሬን ለባሕድ፤ አሳልፈው ሰጥተው
ከሃዲ ሆዳሞች፤ ለባዕዳን አድረው
ውዲቱን አገሬን፤ ለመከፋፈል ቢጥሩም
ኢትዮጵያ አገሬ አትከፋፈልም።

ባገሬ ምድር ላይ፤ ሰላም ካልበቀለ
ዘረኝነት ነግሦ፤ ማቀብ ካልተጣለ
ለምን አልበቀለ፤ ፍትህ እስከሌለ።

ያገራችን ድንበር፤ እስካልተከበረ
ሰንደቅ ዓላማችን፤ መደፈር ካልቀረ
ወገን በእኩልነት፤ በፍትህ ካልኖረ
ሐይማኖታችንም፤ መበረዝ ካልቀረ
ብበቀልም ባስበቅልም አገር ለደፈረ።

ኩነኔም አይደለም፤ ሐራምም አይሆንም
እግዜር አይቀይም፤ አላህ አይቆጣም
ይምስከሩ አባቶች፤ እንዲሁም ሼሆችም
በሁላችን እምነት፤ለይቅርታ አይረፍድም።

አስተምረውናል፤ ገብተናል ቃልኪዳን
በዳይ እንዲናዘዝ፤ የገደለም ቢሆን
ወገኑን የከዳ፤ የሸጠ አገሩን
ይቅርታን ጠይቆ፤ በይፋ ወገኑን
ብቀላ እንዲጠፋ፤ ፍቅር እንዲሰፍን
እናት ኢትዮጵያ፤ ስለምትበልጥብን።
ልጆችሽ አንድ ሁነው እንዲያበለጽጉሽ።

ከጎላምንጭ April 2016